
| | |
|---|---|
| ዐይነት ፤ | ርእስ ፡ አንቀጽ ። |
| ርእስ ፤ | *"እንደ ፡ ስሙ ፡ የሚበተን ፡ "ኢ.-ፌዴሪ" ፡ እንጂ ፥ ኢ.ትዮጵያ ፡ ሀገር ፡ ናትና ፡ አትፈርስም ። "* |
| ደራሲ ፤ | *"ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ።* |
| ዕለት ፤ | *መስከረም ፡ 2014 ፡ ዓ.ም. ።* |
| ዝግጅት ፤ | ፍጹም ። |
| መጽሔት ፤ | *"ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ፥* ቍ.2014-001 |
| ማስታወሻ ፤ | |
| ማሳሰቢያ ፤ | |

# ርእስ ፡ አንቀጽ ።

editorial | éditorial | اِفْتِتاحي

## እንደ ፡ ስሙ ፡ የሚበተን ፡ "ኢ.-ፌዴሪ" ፡ እንጂ ፥ ኢ.ትዮጵያ ፥ ሀገር ፡ ናትና ፥ አትፈርስም ።



ለ 2014 ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ላደረሰን ፡ አምላክ ፡ ክብር ፡ ምስጋና ፡ ይግባውና ፥ ዐዲሱን ፡ ዓመት ፡ በሙሉ ፡ ተስፋና ፡ እምነት ፡ እንቀበለዋለን ።

2013 ፡ ዓ.ም. ፡ ሀገራዊ ፡ ክዳት ፡ ተደጋግሞ ፡ ቢፈጸምባቸውም ፥ የኢ.ትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ እና ፡ ሰራዊት ፡ ተባብረው ፡ በ 80 ፡ ዓመት ፡ ለኹለተኛ ፡ ጊዜ ፡ ፋሺዝምን ፡ ድል ፡ ያደረጉበት ፥ ድላቸውም ፡ በ"ኢ.-ፌዴሪ" ፡ ቅሬታ ፡ ይዘት ፡ የተቀለበሰበትና ፥ ይህ ፡ የሚያጣጥር ፡ የአፓርትሀይድ ፡ ባዕድ-ተኪል ፡ ሥርዐት ፡ በሕፃናትና ፡ በሴቶች ፡ ደም ፡ ዳግም ፡ ሕይወት ፡ ሊዘራና ፡ ሊቆም ፡ የተፈራገጠበት ፡ ኾኖ ፡ ተጠናቅቋል ።

የኢ.ትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ በፋሺዝም ፡ ላይ ፡ የመደምደሚያ ፡ ድሉን ፡ የተቀዳጀበትን ፡ የኅዳር ፡ 18 ፡ ቀን ፡ 1934 ፡ ዓ.ም. ፡ ድል ፡ በ 80 ኛ ፡ ዓመቱ ፡ በ"ኢ.-ፌዴሪ" ፡ ባዕድ-ተኪል ፡ የአፓርትሀይድ ፡ ሥርዐት ፡ ላይ ፡ የሚደግምበት ፡ ዓመት ፡ እንዲኾንለትም ፡ ከልብ ፡ እንመኛለን ።

ፈጣሪው ፡ ምልክዮሽ ፡ (*"ኢ.ምፔሪያሊ.ዝም"*) ፥ ሲፈጥረው ፡ ገና ፥ ለመበተን ፡ የፈጠረውን ፡ "ኢ.-ፌዴሪ" ፥ እንዴት ፡ ፍጡሩ ፡ "ኢ.-ፌዴሪ" ፡ በራሱ ፡ ተጠብቆ ፡ ይድናል ፡ ተብሎ ፡ ይታሰባል ፧ የተፈጥሮ ፡ ሕግ ፡ ነውና ፥ ፈጣሪው ፡ በፈለገው ፡ ጊዜ ፡ ማሰሪያውን ፡ ሳብ ፡ አድርጎ ፡ ይበትነዋል ። የ"ኢ.-ፌዴሪ" ፡ ዕጣ ፡ ፈንታ ፡ ከፈጣሪው ፡ ከምልክዮሽ ፡ በጎ ፡ ፈቃድ ፡ መቼም ፡ መች ፡ አይወጣም ።

ምልክዮሽ ፡ በስግብግብነት ፡ ተፀንሶ ፡ የተወለደ ፣ ያየውን ፡ ኹሉ ፡ *"ለእኔ! ለእኔ ፡ ብቻ!"* ፡ ብሎ ፡ እየነጠቀ ፡ ያፈለ ፡ የጐለበተ ፡ ነጣቂ ፡ ኀይል ፡ ነው ። ምልክዮሽ ፡ በራሱ ፡ ኀይል ፡ ይተማመናል ፤ መተማመን ፡ ብቻም ፡ አይደል ፦ *ከኔ ፡ ወዲያ ፡ ብልጥ ፡ ላሳር ፡ ይላል ።* ዐይነተኛ ፡ ስልቱም ፡ *"ባንድ ፡ ድንጋይ ፡ ኹለት ፡ ወፎችን ፡ መግደል"* ፡ ነው ። ለቅርምት ፡ ዐይኑ ፡ ያረፈባቸውን ፡ ግዛቶች ፡ ራሳቸውን ፡ በራሳቸው ፡ የሚያጠፉበትን ፡ ውስጠ ፡ ተንኰል ፡ ያበጅላቸዋል ፦ *በራሳቸው ፡ ዐቅም ፣ በራሳቸው ፡ ሥርዐት ፣ በራሳቸው ፡ ሰዎች ፡ የራሳቸው ፡ የኾነውን ፡ ዕሴት ፡ ኹሉ ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ ከእጃቸው ፡ ፈልቅቆ ፡ አስጥሎ ፥ ጠባቂ ፡ አልቦ ፡ ሲኾኑ ፥ አላንዳች ፡ ከልካይ ፡ ይቀራመታቸዋል ።* ፈርጠም ፡ ያለ ፡ ባለጋራ ፡ ሲገጥመው ፡ ደግሞ ፥ በዕጥፍ ፡ ኀይል ፡ የሚደመሰሰውን ፡ በዕጥፍ ፡ ኀይል ፡ ይደመስሰዋል ፤ በዕጥፍ ፡ ኀይል ፡ የማይደመሰስለትን ፡ እንደ ፡ ኢ.ትዮጵያ ፡ ያለውን ፡ ሀገር ፡ ደግሞ ፥ በዕጥፍ ፡ ትዕግሥትና ፡ ብልኀት ፣ በዕጥፍ ፡ ተንኰልና ፡ ክፋት ፡ ሸርሽሮና ፡ ገዝግዞ ፣ ሰክሎና ፡ ዘርጥጦ ፡ ይጥለዋል ። ከጣለው ፡ ወዲያም ፥ ያልሞተበትን ፡ ምክንያት ፡ መርምሮ ፡ እስኪደርስበትና ፡ እስኪሸረው ፡ ድረስ ፥ ኹለመናው ፡ ይኰሰተራል ፣ ኅሊናውና ፡ መንፈሱ ፡ ኹሉ ፡ ያተኵርበታል ፤ በማይረግብ ፡ ጽናት ፣ በማይበርድ ፡ እልኽ ፣ በማይራራ ፡ ጭካኔ ፡ እስከ ፡ መጨረሻው ፡ ሊያጠፋው ፡ ይቀጠቅጠዋል ።

ባለፉት ፡ 100 ፡ ዓመታት ፥ ኢ.ትዮጵያ ፡ በዚህ ፡ አስከፊ ፡ የዐጸባ ፡ ምዕራፍ ፡ ዐልፋ ፥ እንሆ ፥ አልሞትለት ፡ ብትለው ፥ ምልክዮሽ ፡ ፍጹም ፡ መሻሪያዋን — ስም ፡ ወደ ፡ ግብር ፡ ይመራል ፡ እንዲሉ — "ኢ.-ፌዴሪ" ፡ ብሎ ፡ አዋቅሮ ፥ በሠራ ፡ አካላቷ ፡ ላይ ፡ ተከለው ፣ በእየሕዋሳቷ ፡ ቸከለው ። የንጹሓን ፡ ልጆቿን ፡ ደም ፡ ለ 30 ፡ ዓመታት ፡ እንደ ፡ ኈረት ፡ አፈሰሰው ። ኢ.ትዮጵያ ፡ ግን ፥ ሀገር ፡ ናትና ፥ አልፈረሰችለትም ፤ ሥልጣኔ ፡ ናትና ፥ አልተገኘችለትም ፤ መንፈስ ፡ ናትና ፥ አልተጨበጠችለትም ፤ በእግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ ውስጥ ፡ ያለች ፡ ምስጢር ፡ ናትና ፥ አልተመረመረችለትም ። ለምልክዮሽ ፡ የቀረው ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ብቻ ፡ ኾነ ፦ በ"ኢ.-ፌዴሪ" ፡ ፍርሰት ፥ የሠራ ፡ አካላቷን ፡ ከፋፍሎና ፡ በላልቶ ፣ ነዳድሎና ፡ ገነጣጥሎ ፡ ማፈራረስ! ዛሬ ፡ እዚህ ፡ አስከፊ ፡ የፍጻሜ ፡ ምዕራፍ ፡ ላይ ፡ ደርሰናል ።


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2014 ፡ ዓ.ም. ።

ትላንት ፡ የኤርትራ ፡ የመገንጠል ፡ "ድንበር" ፡ በደም ፡ ኸፐረት ፡ እንደ ፡ ተሰመረ ፡ ኹሉ ፥ ዛሬ ፡ ደግሞ ፥ የ"ክልሎች" ፡ የመገነጣጠል ፡ "ድንበሮች" ፡ እንሆ ፡ በንጹሓን ፡ ደም ፡ ረስርሰዋል ። አክሊል ፡ የሚደፉበት ፣ የመንገሻቸው ፡ ሰዓት ፡ የደረሰላቸው ፡ የመሰላቸው ፥ የቀድሞ ፡ የመለስ ፡ ዜናዊ ፡ ባለወጎች ፥ የዛሬዎቹ ፡ መንደር ፡ ገነኖች ፥ የ"ክልል" ፡ ዜግነታቸውን ፡ ከኢትዮጵያዊነታቸው ፡ አስበልጠው ፥ ከኢትዮጵያ ፡ "ሕዝቦች" ፡ ውስጥ ፡ የሚመስላቸውን ፡ ለይተው ፡ ሰብስበው ፥ ለመገነጣጠል ፡ ያችን ፡ የምልክዮሽን ፡ የምስጢር-ቃል ፡ ይጠባበቃሉ ።

ለጊዜው ፡ ግን ፥ ሕዝብ ፡ እንዳይገነግን ፥ ምልክዮሽ ፡ ራሱ ፡ የ"ኢ-ፌዴሪ" ፡ ጠላትን ፡ መስሎ ፡ ማስፈራርቾውን ፡ በ CNN ፡ እና ፡ በመሰሎቹ ፡ ማወራኛዎች ፡ ብቅ ፡ ብቅ ፡ በማድረግ ፡ እያስፈራራ ፥ ሕ.ወ.ሐ.ት ፡ የተባለ ፡ "ዞምቢ"ውንም ፡ በንጹሓን ፡ ላይ ፡ በመልቀቅ ፡ በጭካኔ ፡ እያስፈጀ ፥ እስከ ፡ ጊዜው ፡ ጊዜ ፥ ለ"ኢ-ፌዴሪ" ፡ ቅሬታ ፡ ይዘት ፡ የየዋሁ ፡ ሕዝብ ፡ ድጋፍ ፡ እንዲገኝለት ፡ ብሎ ፥ "የሆሊውድ" ፡ ትወናን ፡ በሚያስንቅ ፡ ስብቅልነት ፡ እየተወነ ፥ ሀገርን ፡ ርስ ፡ በርሱ ፡ እያፋጀ ፥ አጥፊውን ፡ "ኢ-ፌዴሪ"ንም ፡ "የሀገር ፡ መከታ" ፡ እያስመሰለው ፡ ከርሟል ። መቼም ፡ ቢኾን ፡ ተላላ ፡ ሰው ፡ አይጠፋምና ፥ ከአራቱም ፡ የዓለም ፡ አግጣጫዎች ፥ በምልክዮሽ ፡ ጉዳይ ፡ አስፈጻሚዎች ፡ የተደለሉና ፡ የተመለመሉ ፡ የዋሃን ፥ በተለይ ፡ በማኅበራዊው ፡ ማወራኛ ፡ እየጻፉና ፡ እየቈፈቈፉ ፦ *መከታችን ፡ ለኾነው ፡ ለ"ኢ-ፌዴሪ" ፡ እናብርለት!* ፡ እያሉ ፡ ሌላውንም ፡ ሲያታልሉና ፡ ሲያሳስቱ ፡ ታዝበናቸዋል ።

የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፥ "ኢ-ፌዴሪ"ን ፡ "መንግሥቴ" ፡ ብሎ ፡ ያቀፈው ፡ ዕለት ፥ በሚቀድለትም ፡ "የክልል ፡ ማንነት" ፡ የመበታተን ፡ ቦይ ፡ ሰተት ፡ ብሎ ፡ የፈሰሰ ፡ ዕለት ፥ የ"ኢ-ፌዴሪ" ፡ ምስጢር-ቃል ፡ ሲሰማ ፥ ያነዬ ፥ ኹሉም ፡ በእየ"ክልሉ" ፡ ይመሰግና ፥ የ"ኢ-ፌዴሪ" ፡ መበተን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብም ፡ መበታተን ፡ እውን ፡ ይኾናሉ ፤ ምልክዮሽም ፡ ሤራው ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ የሰመረለት ፡ ይመስለዋል ።

የሡኔው ፡ ምርጫ ፡ ዋና ፡ ዐላማ ፥ የተጨነቀውንና ፡ ማማረጫ ፡ ያጣውን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፥ ብቸኛውን ፡ ዕጩ ፡ "**ኢ.ሕ.አ.ዴ.ግ.-ብልጽግና ፡ ፓርቲ-ሸኔ**"ን ፡ እንዲመርጥ ፡ በሚያስገድድ ፡ ዐውደ ፡ ኹኔታ ፡ ውስጥ ፡ አስገብቶ ፥ ለሥልጣን ፡ አልቦው ፡ የዶክተር ፡ ዐቢይ ፡ አሕመድ ፡ መንደር ፡ ገነን ፡ አገዛዝ ፡ የሥልጣን ፡ ተገቢነትን ፡ ማስገኘት ፡ ነበር ። ኾኖም ፥ እንደታሰበው ፡ አልተሳካም ። ርግጥ ፡ ነው ፥ ግብዝ ፡ ምርጫ ፡ ተካኺዷል ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ሢሶው ፡ እንኳ ፡ አልተሳተፈበትም ፤ መሳተፍ ፡ ቀርቶ ፥ ለምርጫ ፡ አልተመዘገበም ። የአኃዝ ፡ ንረት ፡ በፈላባት ፡ ኢትዮጵያ ፥ እንደ ፡ "አረንጓዴ ፡ አሻራ" ፡ አኃዞች ፥ የቅጥፈት ፡ አኃዞች ፡ ተነግረዋል ፤ አንዱም ፡ እውነትነት ፡ የለውም ። ይህን ፡ ደባ ፡ የፈጸሙና ፡ ያስፈጸሙ ፥ ከምርጫ ፡ "ቦርድ" ፡ አመራር ፡ አባላት ፡ እስከ ፡ አሯሯጮች ፡ የ"ፖለቲካ ፡ ፓርቲ" ፡ አመራር ፡ አባላት ፥ ኹሉም ፡ ነገ ፡ ጧት ፡ በሕግ ፡ ይጠየቃሉ ።

ዛሬ ፡ ኳሷ ፡ እኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ዘንድ ፡ ናት ። እኛ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፥ ከባዕድ-ተከሉ ፡ የ"ኢ-ፌዴሪ" ፡ የአፓርትሀይድ ፡ ይዘት ፡ ከሞት ፡ በቀር ፡ ምንምን ፡ አይተርፈን ። ይልቅስ ፥ ሳይቀድመን ፡ እንቅደመው ። በሥልጡንሕዝብናችን ፡ ጸንተን ፥ በአንድነት ፡ ቆመን ፡ ይህን ፡ ባዕድ-ተከል ፡ ዲያብሎሳዊ ፡ የ"ኢ-ፌዴሪ" ፡ ይዘት ፥ ሳያጠፋን ፡ በፊት ፦ *"እንቢ! ፡ አንገዛልኽም"* ፡ ብለን ፡ ከነሕገ ፡ ውንብድናው ፡ እንካደው ፣ አሻፈረን ፡ ብለን ፡ ግብር ፡ እንንሣው ፣ ገርስሰን ፡ እንጣለው ፤ ያን ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ሀገራችን ፡ ኢትዮጵያን ፡ እንታደጋታለን ። ነገር ፡ ግን ፥ መገርሰስ ፡ ብቻውን ፡ አይበቃም ፤ **የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ በሙሉ ፡ ነጻነት ፡ ዐዲሱን ፡ ክዋኔውን ፡ ወይም ፡ ሕገ ፡ መንግሥቱን ፡ የሚከውንበትን ፡ የመሸጋገሪያ ፡ መንግሥት ፡ ማቋቋም ፡ ይኖርበታል** ። ይህን ፡ ከራሱ ፡ ከሕዝባዊ ፡ አንድነታዊ ፡ አካሉ ፡ በቀር ፡ ማንም ፡ አይሠራለትምና ፤ **ለዚህ ፡ የተቀደሰ ፡ ዐላማው ፡ ሕዝባዊ ፡ አንድነታዊ ፡ አካሉን ፡ ኢ.ሀ.ሥ.አ.ን ፡ በመቀላቀል ፡ ያዳብረው!**

**ጊዜው ፡ አኹን ፡ ነው ፤ መሣሪያ ፡ ያለኽ ፡ በመሣሪያኽ ፥ ድምፅ ፡ ያለኽ ፡ በድምፅኽ ፣ ብርዕ ፡ ያለኽ ፡ በብርዕኽ ፥ በተሰጠኽ ፡ ጸጋ ፡ ኹሉ ፡ ይህን ፡ ባዕድ ፡ ተከል ፡ የጥፋት ፡ ሥርዐት ፡ ለመገርሰስና ፡ ሀገር ፡ ኢትዮጵያን ፡ ለመታደግ ፡ በአንድነት ፡ ተነሥ! ተደራጅ! ታገል!**

**የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ሆይ! ሥርዐት ፡ ፈርሶ ፡ ዳግም ፡ ይሠራል ፤ ሀገር ፡ ኢትዮጵያ ፡ ግን ፡ ዘለዓለማዊት ፡ ናት ፥ አትፈርስምና ፥ ሥጋት ፡ አይግባኽ ። ሰራዊትኽን ፡ አስተባብረኽ ፥ በግራ ፡ እጅኽ ፡ ወያኔን ፡ አደብ ፡ አስገዝተኽ ፥ በቀኝ ፡ እጅኽ ፡ የ"ኢ-ፌዴሪ" ፡ ቅሬታ ፡ ይዘትን ፡ ለመገርሰስ ፡ ዐይንና ፡ እግርኽን ፡ ወደ ፡ መናገሻ ፡ ከተማኽ ፣ ወደ ፡ ዐዲስ ፡ አበባ** ❖

እግዚአናችንን ፡ የማስከበር ፥
ሕገ ፡ መንግሥታችንን ፡ የመሥራት ፥
ሥልጡንሕዝባዊ ፡ የርትዕ ፡ መንግሥታችንን ፡ የማቆም ፡
ሀገራዊ ፡ ዐላማችንን ፡ ለመፈጸም ፥ በኢትዮጵያና ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ የምንገኝ ፡ ሀገራውያን ፡ ኢትዮጵያውያን ፥ ሕዝባዊ ፡ አንድነታዊ ፡ አካላችን ፡ ለኾነው ፡ ለኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ እናብር!
ኢ.ሀ.ሥ.አ
የኢትዮጵያውያን ፡ ሀገራዊ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ አንድነት ።
ሥልጡንሕዝብና ።
www.slttunhzb.net


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2014 ፡ ዓ.ም. ።